# ገበታዋሪያ፥የንባብ፡መማሪያ።(ደስታ፡ተክለ፡ወልድ።)





ሽፋን-ፊት 1 2 3 4 5 6 7 8 9 10 11 12 13 14 15 16 17 18 19 20 21 22 23 24 25 26 27 28 29 30 31 32 33 34 35 36 37 38 39 40 41 42 43 44 45 46 47 48 49 50 51 52 53 54 55 56 57 58 59 60 61 62 ሽፋን-ዠርባ

# ገበታ ዋሪያ ፥ የንባብ ፡ መማሪያ ።

(ይድረስ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ዦግኖችና ፡ ወጣቶች(ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች) ።

ዐጭር ፡ ያማርኛ ፡ ጓስና ፡ ርባታ ፡ ከነፊደሎቹ ፤

ገና ፡ ካልታተመው ፡ ከታላቁ ፡ ጓስ ፡ ባጭር ፡ ቃል ፡

ተለቅሞ ፡ የወጣ ።

ተረቶችና ፡ ታሪኮችም ፥ ግጥሞችም ፡ አንዳንድ ።

ከደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድ ፡ ዘብሔረ ፡ ወግዳ ፡

በቅዱስ ፡ አልዓዛር ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ — ድሬ ፡ ዳዋ ።

፲፱፻፳፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ።

1935.

፩ኛ ፡ መጣፍ ።

I. S. L.

# ገበታ ዋሪያ ፡ የንባብ ፡ መማሪያ ።

ዐዊ ር ፡ ያማርኛ ፡ ባስና ፡ ርባታ ፡ ከነፊደሎቹ ፤

ገና ፡ ካልታተመው ፡ ከታላቁ ፡ ግስ ፡ ባዊ ር ፡ ቃል ፡

ተለቅሞ ፡ የወጣ ።

ተረቶችና ፡ ታሪኮችም ፡ ግጥሞችም ፡ አንዳንድ ።

ከደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድ ፡ ዘብሔረ ፡ ወግዳ ፡

በቅዱስ ፡ አልዓዛር ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ — ድሬ ፡ ዳዋ ።

፲፱፻፳፰ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ።

1935.

፫ኛ ፡ መጠፍ ።

ዳም ፡ ሙሐንድስ ፡ በስከዋል ፡ ሱራፌ ፡ ባሳየኝ ፡ ፈረማኖች ፡ ይታወቃል ። ከነዚኹም ፡ አንዲቱ ፡ በስላሞች ፡ ቍጥር ፡ ባ፲፻፷፰ ፡ ዓመት ፡ ዚልሕጃ ፡ በሚባል ፡ ባ፲፪ኛ ፡ ወራቸው ፡ ባ፲፯ቀን ፡ የተጻፈች ፡ ናት ። ቃሏም ፡ ይኸ ፡ ነው ። በሲዩስ ፡ የሚባል ፡ የሮም ፡ በትረክ ፡ (ሊቀ ፡ ጳጳስ) ፡ ባ፲፪ ፡ ከ፷፬ ፡ ዓመት ፡ ዚልቂዕዳ ፡ በሚባል ፡ ባ፲ኛ ፡ ወራቸው ፡ ባ፲ቀን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝቦች ፡ ከዳኝነቱ ፡ በታች ፡ ይደሩ ፡ የሚል ፡ ትእዛዝ ፡ ከሥልጣን ፡ ተቀበለ ፡ ትላለች ። እሱም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከቃዲው ፡ የአርመንን ፡ ሕዝቦች ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያሉትን ፡ ሊያቀርብለት ፡ ፈለገ ። የሐበሾችን ፡ ወቅፍና ፡ የሚሰም ፡ በታቸውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸውን ፡ በጎልጎታ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ከውጪም ፡ ያለውን ፡ በጃቸው ፡ የያዙትን ፡ ኹሉ ፡ በሥልጣን ፡ ትእዛዝ ፡ ለቀው ፡ ለርሱ ፡ ያስረክቡ ፡ ዘንድ ። አገሬ ፡ ገዥውም ፡ በዚያው ፡ ጊዜ ፡ ኹላቸውን ፡ የአርመኖችን ጳጳስ ፡ ወኪል ፡ ትርጁማናቸው ፡ የሚኸን ፡ የኸዘርን ፡ ልጅ ፡ ያዕቆብን ፡ አቀረበለት ። ትእዛዙን ፡ ከነበበላቸው ፡ በኋላ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የነበረውን ፡ ኹሉ ፡ በጃችኹ ፡ ያለውን ፡ ለሮም ፡ አስረክቡ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ። ወዲያው ፡ የመንግሥት ፡ ሹማምቶች ፡ ወደ ፡ ጎልጎታ ፡ ሄዱ ፤ የሮሞች ፡ ትርጁማን ፡ አብራሂም ፡ በጎልጎታ ፡ ከሚኖረው ፡ ከሰርኪስ ፡ ከአርመኑና ፡ ከወገኖቹ ፡ በሹማምቱ ፡ ፊት ፡ ተረከበ ። ከጓንዘቱ ፡ ላይ ፡ ቀንዲል ፡ የሚሰቀልበትን ፡ ቦታ ፡ ከመቃብሩ ፡ ውስጥ ፡ ፯ቀንዲል ፡ የሚሰቀልበትን ፡ ቦታ ፤ ከመቃብሩም ፡ ውጪ ፡ ፪ቀንዲል ፡ የሚሰቀልበትን ፡ ቦታ ፤ አንዱ ፡ በሰሜን ፡ አንዱ ፡ በደቡብ ፤ ፫ቱንም ፡ ጓዳዎች ፡ ለሐበሾች ፡ ብቻ ፡ የነበሩትን ፤ በቤተ ክርስቲያኑ ፡ ደቡብ ፡ ያሉትን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንነት ፡ የታወቁትን ፡ በውስጣቸውም ፡ ያሉትን ፡ የብርጭቆ ፡ ቀንዲሎች ፤ በሰሜንም ፡ ያሉትን ፡ ፪ጓዳዎች ፡ እነሱን ፡ ተጠግቶ ፡ የታነጠውንና ፡ የተጌጠውን ፡ ዕንጨት ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ያለውን ፤ በምሥራቅም ፡ ያለውን ፡ መቅደስ ፡ የሐበሾች ፡ መኾኑ ፡ የታወቀውን ፡ የታነጠ ፡ ዕንጨት ፡ በስተደቡብ ፡ በአንጻሩ ፡ ያለውን ፤ በምሥራቅና ፡ በደቡብ ፡ መካከል ፡ ያለውንም ፡ መቅደስ ፡ መንበሩ ፡ በሚሳለሙት ፡ ዐምድ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፤ በውስጡም ፡ ያሉትን ፡ የብርጭቆ ፡ ቀንዲሎች ። ደጃፉ ፡ የታነጠ ፡ የተበሳሳ ፡ ዕንጨት ፡ የኾነውን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ያለውን ፤ ይኸ ፡ ኹሉ ፡ ከጎልጎታ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ኹሉንም ፡ ጨርሰው ፡ ወሰዱ ። በጎልጎታ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ለነበሩ ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ሰዎች ፡ ከብር ፡ ቀንዲልና ፡ ከብር ፡ መስቀላቸው ፡ ከንዋየ ፡ ቅድሳታቸው ፡ ኹሉ ፡ ምንም ፡ አልቀረላቸው ። ሐበሾች ፡ ፯ቀንዲል ፡ ይሰቅሉበት ፡ በነበረው ፡ ቦታ ፡ ሮሞች ፡ ከራሳቸው ፡ ፳ ፡

(ለ)—ሌባሻይ ። በንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ጊዜ ፡ ሽፍታ ፡ እጅግ ፡ በዝቶ ፡ ነበር ። ከሽፍቶቹም ፡ አንዱ ፡ ዋነኛው ፡ ንግዴ ፡ ይባላል ። ሣህለ ፡ ሥላሴም ፡ የንግዴ ፡ ነገር ፡ ስላስፈራቸው ፡ አትርሱኝ ፡ ሲሉ ፡ ወደ ፡ ገዳማቱ ፡ ኹሉ ፡ ገንዘብ ፡ ላኩ ። ከመነኰሳቱም ፡ አንዱ ፡ መነኵሴ ፡ ሲያሳርጉ ፡ ንግዴም ፡ ዳር ፡ ዳሩን ፡ ያነጥንጥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴም ፡ ከልጋው ፡ አይናወጥ ፡ ብለው ፡ አሳረጉ ። ይኸነንም ፡ ያሉበት ፡ ምክንያት ፡ ንግዴም ፡ በበኩሉ ፡ እየዘረፈ ፡ የሚሰጣቸው ፡ ስለ ፡ ኸነ ፡ ነው ። ንጉሡም ፡ የሽፍታና ፡ የሌባ ፡ ነገር ፡ ቢያስቸግራቸው ፡ ከባለሟሎቻቸው ፡ ጋራ ፡ መክረው ፡ የሌባሻይን ፡ ብልኀት ፡ አወጡ ፤ ብልኀቱም ፡ እንዲኸ ፡ ነው ። ባላገር ፡ ኹሉ ፡ በያገሩና ፡ በየመልከኛው ፡ በየባላባቱና ፡ በየገጠሩ ፡ አገር ፡ የሚያውልና ፡ የሚጠብቅ ፡ ስሙን ፡ የጕልማሳ ፡ ጌታ ፡ እያለ ፡ አንዳንድ ፡ ሰው ፡ ይሾም ፡ ነበር ። ሽማግሎችና ፡ አማካሪዎች ፡ መርማሪዎችም ፡ ይመረጣሉ ። እነዚኸም ፡ ኹሉ ፡ ሌባዉንና ፡ ቀጣፊዉን ፡ ሽፍታዉንና ፡ ወንበዴዉን ፡ በውነት ፡ መርምረው ፡ ይይዙና ፡ ለጕልማሳ ፡ ጌታ ፡ ይሰጣሉ ። (ወዮ ፡ ይኸች ፡ ብልኀት ፡ ምንኛ ፡ ድንቅ ፡ ናት! ፤ አባት ፡ ልጁን ፡ አይምርምና) ። ነገር ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ ሌቦችና ፡ ቀጣፎች ፡ ካንዱ ፡ አገር ፡ ወዳንዱ ፡ አገር ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ቀን ፡ ሲኼዱ ፡ ይውሉና ፡ ማታ ፡ መሸቶ ፡ ጨለምለም ፡ ሲል ፡ ሰርቀው ፡ ቀምተው ፡ ሌሊቱን ፡ ገሥግሠው ፡ ጧት ፡ በቤታቸው ፡ ይገኛሉ ። ሌብነታቸው ፡ እየታወቀ ፡ ሲይዟቸው ፡ ዐሰት ፡ አልሰረቅንም ፤ ርቱን ፡ እያሉ ፡ ያስቸግሩ ፡ ነበርና ፤ የጕልማሳ ፡ ጌታ ፡ ከሽማግሎቹና ፡ ከማካሪዎቹ ፡ ከመርማሪዎቹም ፡ ጋራ ፡ ኹኖ ፡ ለሌባሻዉ ፡ ሌባዉን ፡ ይጠቍመዋል ፤ ሌባው ፡ የተያዘ ፡ እንደ ፡ ኸነ ፡ የተሰረቀው ፡ ዕቃ ፡ ይገኛል ፤ እሱም ፡ ሌብነቱን ፡ ያምናል ። ስለዚኸ ፡ ሌባሻይ ፡ ለጊዜው ፡ እውነተኛ ፡ መሰለ ፤ ስሙም ፡ የንጉሥ ፡ ቍና ፡ ተባለ ። በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ የነበረው ፡ ሌባሻይ ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ ገንዘቡ ፡ የጠፋበትን ፡ ሰው ፡ ጠላትኽ ፡ ማነው ፤ የምትጠረጥረውስ ፡ ማነው ፡ እያለ ፡ ባልሰረቀው ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ እያስተኛና ፡ ያልሰረቀውን ፡ እየያዘ ፡ ሰውን ፡ የሚጐዳና ፡ የሚያታልል ፡ መኾኑን ፡ ስላወቁ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ዐልጋ ፡ ወራሽ ፡ ልዑል ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ በንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ጊዜ ፡ ይቅር ፡ ብለው ፡ አስቀሩት ። አገራችንም ፡ ከታላቅ ፡ አደጋ ፡ ዳነች ። በሌባሻይ ፡ ምክንያት ፡ ቤታቸውን ፡ የተወረሱና ፡ ትዳራቸውን ፡ ያጡ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። ሌባሻይ ፡ ምንም ፡ ቢኸን ፡ ከፈረንጅ ፡ ቤት ፡ አይገባም ፡ ነበር ። ኹል ፡ ጊዜም ፡ በውሃ ፡ ይታጠባል ፤ ይኸም ፡ ዋና ፡ ማታለያው ፡ ነው ። (፲፫ኛ ፡ ሥዕል)

(ነ)—ነብር ። ነብር ፡ በዱር ፡ የሚኖር ፡ መልክ ፡ ዥጕርጕር ፡ የድመት ፡ ወገን ፡ አው

ያዘንምባቸዋል ፡ እሳት ፡ ኤልያስ ፡ ሰናድሮኽ ።
ጣሊያንንሂ ፡ የማሽላ ፡ እሸት ፡ እንድታበላው ፡ ጠብሰኽ ፡
ምኒልክ ፡ ያ ፡ ደገኛ ፡ ይመጣልና ፡ ወደ ፡ ቤትኽ ።
አምጥተኽ ፡ ቈየው ፡ በፊት ፡ ራስ ፡ ራሱን ፡ ቈርጠኽ ።
አገዳውንስ ፡ ይመጡታል ፡ እየሰባበሩ ፡ አሽከሮችኽ ።

«ወኵሎ ፡ ዘተብህለ ፡ በእንተ ፡ አብ ፡ ርቱዕ ፡ ያምጽኡ ፡ ኀበ ፡ ወል
ድ ፤ እስመ ፡ ዘይገብር ፡ አብ ፡ ወልድኒ ፡ ኪያሁ ፡ ይገብር ፡ በአምሳሉ ፤ ወ
ዘየዐቢ ፡ ግብረ ፡ ሀለዎ ፡ ያርኢ ፡ ለኵሉ ፡ በጽንዐ ፡ ኀይሉ» ።

ዓዲ ፡ መወድስ ፡ ካልእ ፡ በእንተ ፡ መቅበርቱ ፡ ወተዝካረ ፡ሞቱ ፡ ለ
ዝንቱ ፡ ልዑል ፡ እምልዑላን ፡ ወርእሰ ፡ ርኡሳን ፡ ዘቡሩክ ፡ ዝክሩ ፡ እም
ንእሱ ፤ ወቡሩክ ፡ ዘርዑ ፡ ወፍሬ ፡ ክርሡ ።

ሚካኤል ፡ ቤትከ ፡ ቤተ ፡ አብርሃም ፡
እስመ ፡ እምትክት ፡ ውእቱ ፡ ማኅደረ ፡ ፈላሲ ፡ ወነግድ ።
ወድንግለ ፡ሙሴ ፡ ፍቅርከ ፡ እመ ፡ ወልደ ፡ አምላክ ፡ ዋሕድ ፤
አመ ፡ ዕለተ ፡ ሞት ፡ ወሊዶታ ፡
ጥብሉለ ፡ እስመ ፡ አስከቦቶ ፡ ውስተ ፡ ዝ ፡ ዐጸድ ።
ሕገ ፡ ሰብእናሁ ፡ ከመ ፡ ታግህድ ፡
ለተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዮሴፍ ፡ አበ ፡ ብዙኃን ፡ ውሉድ ።
እግረ ፡ ፀርሂ ፡ መቃብሪሁ ፡ ከመ ፡ ኢይኪድ ፡
መብረቅ ፡ እምየማንከ ፡ ወእምፀጋምከ ፡ ነጐድጓድ ።
ወኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዐይንከ ፡ ዐይነ ፡ ርግበ ፡ ሰማይ ፡ ውዱድ ፡
ለምድረ ፡ አሕዛብ ፡ ይኔጽራ ፡ ወይሬስያ ፡ ከመ ፡ ትርዐድ ።

፲፱፻፳፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ግንቦት ፡ ፲፪ ።

ኪ ፡ ወ ፡ ክ ፨

